የካቲት 2003 ዓ.ም.

# 1968 ዓ.ም.አዶሓ ኢሮቢህ አግለ ቦካለማኮል/ዓሊተናል .

## ትርጉም፤ የ1968 ዓ.ም. የኢሮብ ስብሰባ በቦካለማኮ/ዓሊተና

**ከበየነ ገብራይ**

በ1968 ዓ.ም. የአጠቃላይ ኢሮብ ተወካዮች የተገኙበት ታሪካዊ ስብሰባን በሚመለከት የማውቀውን ለመጻፍ ያነሳሱኝ ሶስት መሰረታዊ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው። እነሱም፣

1ኛ. የኢሮብ ህዝብ የፈለሰው ከጎረቤቱ ከትግርኛ ተናጋሪ ህዝብ ነው የሚል በጽሁፍና በቪድዮም ተቀርፆ መውጣቱን በማየቴ።

2ኛ. ለጽሁፌ የቦካለማኮ የኢሮብ ተወካዮች ስብሰባ የሚለው ርእስ እንድሰጠው ምክንያት የሆነኝ በቅርቡ በምስአል ቢዝነስን እንዱስትርን የሚባል የግል ማህበር ስፖንሰር ተደርጎ በአቶ ፀጋው ታደሰ በትግርኛ በተተረከው የኢሮብ ህዝብ ታሪክ ውስጥ አቶ ፀጋው ታደሰ የኢሮብ ህዝብ ገና ከጅምሩ ኢህአፓና ህወሓትን እኩል ተቀብሎ አስተናገዶአቸዋል የሚለው የተሳሳተ ዘገባ በመቅረቡ።

3ኛ. ትናንትና በኛ ዕድሜ የተደረጉ ታሪካዊ ክንዋኔዎች ተንሸዋርረው ከፖሊቲካዊ አመለካከት ጋር በማቀናጀት እየቀረቡ እንደሆነ ስለተገነዘብኩ ነው።

እኔ የኢሮብ ህዝብ ጥንታዊ ታሪክ አስፈላጊ ምርምር፣ በቂ ጥናት ተደርጎበት፣ መሰባሰብ የሚገባቸው ማስረጃዎች፤ መረጃዎችና ቁሳቁሶች ተሰብስበው መጻፍ አለበት የሚል የጠና እምነት ስላለኝ ነው ። ይህን የጥንት ታሪክ የማሰባሰብና መጻፍ ስራ ዕውቀቱና ችሎታው ላላቸው በመተው እኔ ይበልጥ በሚያሳስበኝ የኢሮብ ህዝብ አሁን ያለበት ሁኔታና ራሴ የተሳተፍኩበትና የማውቀውን ታሪክ በመናገር ላይ አተኩራለሁ።

ለዛሬ ልጽፍበት ወደተነሳሁበት የቦካለማኮ የ1968 ዓ.ም. ስብሰባ ትረካ ከመግባቴ በፊት ይህ ስብሰባ እንዲደረግ ምክንያት ስለሆነው በ1966 ዓ.ም. ማብቂያ ላይ በሞላው ኢትዮጵያ የተቀጣጠለውና የአፄ ኃ/ስላሴ ዘውዳዊ አገዛዝን ሙሉ ለሙሉ ገርስሶ ስላስወገደው ሰላማዊ ህዝባዊ አመጽና በወቅቱ ስለተፈጠሩ የፖሊቲካ ድርጅቶች ባጭሩ ለግንዛቤ እንዲረዳ ትንሽ ልበል። ሁላችን እንደምናስታውሰው በተማሪዎች ደረጃ በተለይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለረጅም ዓመታት ሲካሄድ የቆየው የተማሪው ጸረ ዘውዳዊ አገዛዝ ትግል ወደ ህዝቡም ተሸጋግሮ በ1966 ዓ.ም የኢትዮጵያ ህዝብ ዘውዳዊ አገዛዝ ያብቃ ብሎ መነሳሳቱ የሚታወቅ ነው። በዚህ በ1966 ዓ.ም. ህዝባዊ አብዮት ህዝቡ ይዞዋቸው ከተነሳ መፈክሮች፣ ህዝባዊ መንግስት ይመስረት፣ መሬት ለአራሹ፣ የብሄረሰቦች መብት ይከበር፣ የሃይማኖት እኩልነት

ይኑር የሚሉ ዋና ዋናዎቹ ነበሩ። ህዝቡ እነዚህን መፈክሮችን አንግቦ በተለይ የሀገሪቷ መዲና በሆነችው አዲስ አበባና በተለያዩ የሀገሪቱ ትልልቅ ከተሞች ተነስቶ በዚህ ህዝባዊ አመጽም አፄ ኃይለስላሴ ከ40 ዓመት በላይ ይዘዉት ከነበረው ስልጣናቸው እንዲወገዱ አድርጓል። በ1966 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ህዝብ ለመብቱ ለመታገል ቆርጦ የተነሳበት ወቅት የነበረ ቢሆንም በወቅቱ የተደራጀ ብቃት ያለው የህዝቡን ትግል ሊመራ የምችል የፖሊቲካ ድርጅት እንዳልነበረም በወቅቱ የነበረው ትውልድ ሁሉ የሚያስታውሰው ሃቅ ነው። ስለሆነም በወቅቱ ተደራጅቶ የነበረው ወታደር ብቻ ስለነበረ ጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ በሚል በትረስልጣኑን በመያዝ ህዝባዊ አመጹን መቀልበሱ ይታወሳል። በትረ ስልጣኑን በጊዜያዊነት ስም በመያዝም ለ17 ዓመታት የኢትዮጵያን ህዝብ ከ1967 እስከ 1983 ዓ.ም. በፋሽታዊ አገዛዝ እንደገዛ የትናትና መራራ ትዝታችን ነው። ይህ በእንዲህ እያለ ከኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ የሚወለዱት እንደ ኢህአፓ፣ ማ.ገ.ብ.ት. በኋላ ወደ ተሓህት የተቀየረው የመሳሰሉ ድርጅቶች የሚመመሰረቱም በዚህ በ1966 ዓ.ም. ወይም ትንሽ ቀደም ብሎ ነው፡ በተለይ የኢህአፓ ምስረታን ከተመለከትን ደግሞ እንደ ድርጅት የተመሰረተው በ1964 ዓ.ም. ነው።

ሁለቱም ኢህአፓና ማ.ገ.ብ.ት. የደርግ ፋሽታዊ አገዛዝ በሰላማዊ ትግል ብቻ ሊወደወቅ እንደማይችል ወስነው የትጥቅ ትግል በ1967 ዓ.ም. ጀምረዋል። ኢህአፓ የትጥቅ ትግልን በኢሮብ/ዓሲምባ ሲጀምር፣ ማ.ገ.ብ.ት ደግሞ በሽሬ/ደደቢት ላይ ጀመረ።

1. ኢህአፓ የትጥቅ ትግሉን ለምን በኢሮብ/ዓሲምባ ጀመረ?
2. ህወሓትስ ለምን በደደቢት ትጥቅ ትግሉን ለመጀመር መረጠ?
3. የያኔው ተሓህት የዛሬው ህወሓት መቼ ነው ከደደቢት ወደ ኢሮብ መሬት የዘለቀው?
4. እውነት ተራኪ አቶ ፀጋው ታደሰ እንደሚሉት የኢሮብ ህዝብ ኢህአፓንና ተሓህትን እኩል ተቀብሎ አሰተናግዶዋቸዋል ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች እያንዳንዳቸው መጻህፍት ሊጻፍባቸው የምችሉ ትልልቅ ጥያቄዎች ናቸው።

ሌሎቹን በይደር በመያዝ ለዛሬው በቀጥታ ከዚህ የቦካለማኮ ታሪካዊ የኢሮብ ህዝብ ስብሰባ ቀጥተኛ ግኑኝት ያለው እውነት የኢሮብ ህዝብ ኢህአፓንና ህወሓትን እኩል ያውቃቸዋል ወይ? አቶ ፀጋው ታደሰ እንደሚሉት ገና ከጅምሩ እኩል ተቀብሎ አስተናግዶአቸዋል ወይ? የሚሉትን ጥያቄዎች እኔ እንደማውቀው ለታሪክ እንዲቀመጥና ከዛ በኋላ የተወለደው ትውልድ እንዲያወቅ የማውቀውን እንደሚከተለው አስቀምጣለሁ።

## የኢሮብ ህዝብና የኢህአፓ ግኑኝነት መቼና እንዴት ተጀመረ? የያኔ ተሓህት ያዘሬ ህወሓትስ መቼ ነው ወደ ኢሮብ አከባቢ የመጣው?

በኢሮብ ህዝብ አጠራር ዓሲምባ በመባል የሚታወቀው ኢህአፓ በኢሮብ ህዝብ ውስጥ ድርጅታዊ ስራ መስራት የጀመረው ገና በ1966 ዓ.ም. መጀመሪያ ጀምሮ ነበር። ዛሬ በህይወት የሌለው ዶክተር ተስፋይ ኃይለማሪያም/ቀያፋ ገና 1966 ሀ ብሎ ሲጀምር ለዚህ ድርጅታዊ ስራ ተመድቦ ኢሮብ ውስጥ በተለያዩ አከባቢዎች ድርጅታዊ ስራ ሲሰራ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም በተለይ የትጥቅ ትግል ለመጀመር የተመደበው የኢህአሠ ጀማሪ ቡድን አስፈላጊ የሰው ሃይልና የስንቅ ዝግጅትም ሲያደርግ ነበር። ከዶክተር ተስፋይ ኃ/ማርያም

በተጨማሪም በኢሮብ ህዝብ ውስጥ ከፍተኛ ተሰሚነት የነበረው ገረይ ተስፋይም ይህን ድርጅታዊ ስራ ለማጠናከር ገና የትጥቅ ትግል ጀማሪ ቡድን ወደ ኢሮብ ከመምጣቱ በፊት በወቅቱ ሲሰራው የነበረ የአስተማሪነት ስራዉን አቋርጦ እዛው ኢሮብ ውስጥ ድርጅታዊ ስራ ይሰራ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ በ1985 ዓ.ም በአዲስ አበባ በኢህአዴግ የጸጥታ ሃይሎች የተገደለው ገብረእግዚአብሄር (ጋይም) ኃይለሚካኤል ዓዲግራትን ማእከል በማድረግ ገና ከ1966 ጀምሮ በዓዲግራት በትምህር ላይ ከነበሩ የኢሮብ ተማሪዎች መካከል ለኢህአፓ አባልነት ሲመለምልና ሲያደራጅ ነበር። በዚህ የተነሳም በርካታ የኢሮብ ወጣቶች ገና የኢህአፓ ትጥቅ ትግል ጀማሪ ቡድን በ1967 ዓ.ም. ወደ አከባቢው እንደመጣ እንዲቀላቀሉት ሆነዋል።

የያኔው ተሓህት የዛሬው ህወሓት ወደ ዓጋሜ አውራጃ መምጣት የጀመረው በ1968 ዓ.ም. የመጀመሪያ አጋማሽ ውስጥ ነው። ህወሓት ወደ ኢሮብ አከባቢ ከመምጣቱ በፊት በአከባቢው በትግራይ ስም የተደራጀ ተ.ሓ.ት/ተጋድሎ ሓርነት ትግራይ የሚባል ድርጅት በተለይ የአድጋዲዓረ አከባቢን ማእከል በማድረግ ይንቀሳቀስ ነበር። ተ.ሓ.ት. በኋላ በ1968 በዛጋብላ የተወሰኑ አባላቱ በህወሓት ተገድለው ሌሎች ተማርከው ባጭር ጊዜ ውስጥ በህወሓት ተውጦ ከታሪክ ውጭ ሆኗል። ህወሓት ምንም እንኳን ወደ ዓጋሜ አውረጃ የዘለቀው በ1968 ዓ.ም. ቢሆንም እስከ 1969 ዓ.ም. በጣም ከተወሰኑ ግለሰቦች ጋር ካልሆነ በስተቀር ከኢሮብ ህዝብ ጋር ልክ ኢህአፓ/ሠ የነበረው ዓይንት ሰፊ ግኑኝነት ከህዝቡ ጋር ፈጽሞ አልነበረውም።

ከላይ ባጭሩ ለማሳየት እንደሞከርኩት ኢህአፓ ከህዝቡ ውስጥ ድርጅታዊ ስራ በመስራቱ፣ ከራሱ ከኢሮብ ህዝብ የተወለዱ በርካታ አባላት ስለነበሩት፣ በጣም የሚከበሩና የሚወደዱ እንደነ ዶክተር ተስፋይ ደበሳይ፣ ዶክተር ተስፋይ ኃይለማሪያም፣ ገረይ ተስፋይ.... የመሳሰሉ በድርጅቱ ውስጥ በአመራርነትም በአባልነትም ስለነበሩ፣ ኢህአፓ እታገላለሁ ብሎ የተነሳው አጠቃላይ ጭቆናን ከኢትዮጵያ ለማስወገድ የሚል ስለነበረ በወቅቱ በኢሮብ ህዝብ ተቀባይነት አግኝቶ ነበር። ሌላም ኢህአፓ በአከባቢው በህዝቡ መካከል መንቀሳቀስ ሲጀምር መጀመሪያ የህዝቡ መሰረታዊ በወቅቱ የነበሩ ችግሮች ለመፍታት መቻል ሌላው ለኢህአፓ በህዝቡ ተቀባይነንት እንዲያገኝ አስችለውታል። በአብዛኛው ህዝብ እንዲታቀፍ ካስቻሉት በኢህአፓ/ሠ በወቅቱ ከተወሰዱት እርምጃዎች ዋነኞቹ ሁለት ነበሩ።

1ኛ. በአከባቢው እየተስፋፉ ሂዶ የነበረውን ሌብነት ማስቆም

2ኛና ዋነኛው ደግሞ መሬትን አልባ ወጣት አርሶ አደሮች መሬት እንዲያገኑ ማድረግ ናቸው።

ተራ የፍየልና የበግ ሌቦችን ለማስቆም ብዙ ችግር አልፈጠረም። በየአከባቢውን ሌቦቹ እነማን እንደነበሩ ህዝቡ በሚገባ ያወቅ ስለነበረ የእነዚህ ሌቦች የስም ዝርዝር በሚስጥር ለኢህአሠ በመስጠት በቀላሉ እንዲቆሙ ተደረገ። መሬት ለብቻቸው ይዘው የነበሩ አርሶ አደሮችን አሳምኖ ለወጣት አርሶ አደሮች በፈቃደኝነት እንዲያከፋፍሉ የማሳመን ስራ ግን ትልቁ ፈተናና ብዙ ስራ የጠየቀ ነበር።

ይህ የመሬት ማከፋፈልና ወጣቶቹ የራሳቸው የሆነ የእርሻ መሬት እንዲያገኙ የማድረግ ስራ ጥናት የሚጠይቅ፣ በተቻለ መጠን መሬቱን የያዙ አባቶችን አሳምኖ መሬቱ እንዲከፋፈል ለማድረግ ወደ አንድ ዓመት ያህል ጊዜ የወሰደና ብዙ ቅስቀሳና ስራ የጠየቀ ነበር። መሬት በኢሮብ ወረዳ መከፋፈል እንዳለበት በሁሉም ከታመነበት በኋላ እንዴት መተግበር እንዳለበት እንዲያጠናና እንዲሰራ ሃላፊነቱ በኋላ በደርግ አፋኞች ለተገደለው ለአቶ ገረይ ተስፋይ ተሰጠ። አቶ ገረይ ተስፋይ በአጠቃላይ የኢሮብ ህዝብ ዘንድ በትልቁም በትንሹም ሁሉ የሚከበር፣ ሀቀኛ የህዝብ ልጅ ስለነበረ በቡክናይቲዓረ፣አድጋዲዓረና ሓሳባላ በመዘዋወር አንዳንድ ቅሬታ የነበራቸው ባለመሬቶችን በየግልም በቡድንም በማነጋገር በነሱም ዘንድ እንዲታመንበትና ተቀባይንት እንዲያገኝ አደረገ። ከዚህ በኋላ ለወጣት አርሶአደሮች መሬት የማከፋፈል ስራ በኢሮብ ደረጃ የኢሮብ ተወካዮች የሚገኙበት ስብሰባ የኢሮብ ህዝብ ማእከል በሆነችው በዓሊተና እንዲጠራ ተወሰነ።

## ለምን ስብሰባው ዓርበይታን (ዓሊተና) ትቶ በቦካለማኮ እንዲሆን ተፈለገ?

ከጥንት ከጥዋቱ የ3ቱ ኢሮብ ጉዳይ የሚመለከቱ ስብሰባዎች ይደረጉ የነበሩት በዓሊተና እንደነበረ አባቶቻችን እየነገሩን ያደግንበት ነው። በዚህ የኢሮብ ህዝብ እምነት መስረት ስብሰባው ከዓሊተና መውጣት እንደሌለበት በሁሉም ታመነበት። ይህ የ1968ቱ የ3ቱ ኢሮብ ተወካዮች ስብሰባ ከዓሊተና/ዓርበይታ ትንሽ ወጣ ብሎ በቦካለማኮ እንዲካሄድ የተደረገበት ብቸኛ ምክንያት ቦካለማኮ ከዓሊተና/ዓርበይታ በርከት ያሉ ለጥላ የሚያመቹ ዛፎች ያሉበት ቦታ በመሆኑ ነበር።

## በጉባኤው የተገኙ ተሳታፊዎች ብዛትና ዓይንት ምን ይመስል ነበር?

በዚህ ታሪካዊ ስብሰባ አዱሓ ኢሮብ፣ ትርጉም ሶስቱ ኢሮብ በትክክል የተወከሉበት፣ ከሁሉም የዕድሜ ክልል የሚገኙ ከዕድሜ ባለጸጎች እስከ ወጣት አርሶ አደሮች በሚገባ የተወከሉበት፣ በኢሮብ ህዝብ ውስጥ በተግባራቸው አንቱታን ያተረፉ ታዋቂ ግለሰቦች የተገኙበት ስብሰባ ነበር።በስብሰባው ከተገኙት ታላላቅ የዕድሜ ባለጸጋና አንቱታን ካተረፉ ታላላቅ አባቶች እንደ ያባ ዓዶዑማር ሐሊቦ (ጎዒስ) ከዓሊተና፣ ኦና ወልደገርጊስ ወልዱ ከዓይጋ፣ ልጅ ንጉሠ ወልደገርጊስ ከማጋዑማ የመሳሰሉ በግንባር ቀደምትነት ሊጠቀሱ ከምችሉት ውስጥ ነበሩ። በርግጥ በውክልና ደረጃ ሁሉንም ያሳተፈ ቢሆንም ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት መሬት እንዲሰጣቸው ይፈልጉ የነበሩ ወጣት አርሶ አደሮች ነበሩ። ከዚህ በተጨማሪም በመካከለኛ ዕድሜ ላይ የነበሩ፣ የመሬት ባለንብረት የነበሩ አርሶ አደሮችም ቁጥራቸው ቀላል አልነበረም። በአጠቃላይ የነበረው የተሰብሳቢ ብዛት ያለማጋነን ከ300 በላይ ሰው ነበር።

## የስብሰባው አካሄድ ስነስርዓት

ስብሰባው የተመራው በአቶ ገረይ ተስፋይ ነበር። ስብሰባው ትክክለኛ የኢሮብ ባህላዊ ዴሞክራሲያዊ አካሄድን የተከተለ ነበር።ታላላቆች፣ አዋቂዎች በመጀመሪያ ምን ቢሆን ይሻላል በሚለው በተለይ ባለመሬቱን እና መሬት ፈላጊ ወጣቶችን ሊያግባቡ የምችሉ ሃሳቦችን

በመስጠት ነበር የተናገሩት። በዚህ ላይ ያባ ዓዶዑማር ሐሊቦና ኦና ወልደገርጊስ ወልዱ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱበት ሁኔታም ነበር።

ከነዚህ የዕድሜ ባለጸጋና አዋቂ አባቶች ምክርና መወሰድ ባለባቸው ውሳኔዎች ላይ ሃሳብና አሰተያየተ ከተሰጠ በኋላ መድረኩ ለመሬት ፈላጊ ወጣቶች ተከፍቶ ከተለያዩ ቦታዎች የመጡ ወጣት አርሶ አደሮች መሬት ባለማግኘታቸው ምን ያህል ችግር እንዳለባቸው በስፋት እንዲገልጹ ተደረገ። በመጨረሻ ሰፋፊ መሬትን የያዙ የተወሰኑ አርሶ አደሮች እንዴት ከያዙት መሬት የተወሰነውን ለወጣቶቹ ማከፋፈል እንደሚችሉ፣ እነሱ ምን ያህሉን መሬትይዘው መቅረት እንዳለባቸው በመዘርዘር ሃሳባቸውን እንዲሰጡ ተደረገ።

በዚህ መልክ ሁሉም ሃሳቡን ከሰጠ በኋላ አቶ ገረይ ሃሳቦቹን አጠቃልሎ በማቅረብ አሁን ወደ ተግባራዊ መፍትሄ ሰጪ ውሳኔዎች እንጓዝ በማለት ሃሳብ አቀረበ። በዚህ ጊዜ ያባ ዓዶዑማር ሓሊቦ ባለመሬቶቹን ለወጣቶቹ መሬት በፍላጎት ለማካፈል መፍቀዳቸውን አመስግነው፣ ወጣቶቹን ደግሞ ሁኔታዎችን ረጋብለው እንዲመለከቱዋቸው መክረው የሚከተሉትን የውሳኔ ሃሳቦች አቀረቡ።

የውሳኔ ሃሳቦቹም፣

1. የመሬት አከፋፋይ ኮሚቴዎች ከባለመሬቶቹ፣ ከወጣቶቹና ከኢህአፓ የብዙሃን ድርጅት ተወካዮች ያለበት ሆኖ በየአከባቢው የገበሬ ማህበራት እንዲቋቋሙ
2. ለነዚህ መሬት አከፋፋይ ኮሚቴዎች ሁሉ የሚሆን መመሪያ በዕለቱ የስብሰባው መሰረታዊ እምነቶች መሰረት በአቶ ገረይ ተስፋይ እንዲዘጋጅና ለሁሉም መሬት አከፋፋይ ኮሚቴዎች እንዲሰጥ በማለት ሃሳብ አቀረቡ። ይህ ያባ ዓዶዑማር ሓሊቦ ሃሳብ የተወሰነ ውይይት ከተደረገበት በኋላ በተሰብሳቢው ሙሉ ስምምነት ጸደቀ።

## ሁለት የተሓህት ታጋዮች ወደ ጉባኤው ቦታ/ቦካለማኮ መምጣት

የያኔው ተሓህት የዛሬው ህወሓት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ዓጋሜ አውራጃ በአጠቃላይ እንደ ታጠቀ ሃይል መዝለቅ የጀመረው ከላይ እንዳስቀመጥኩት በ1968 ዓ.ም. መጀመሪያ አከባቢ ነበር። በኢሮብ ወረዳ ግን ተሓህት በርከት ያለ ህዝብ በተሰበሰበበት ስብሰባ በመገኘት ዓላማውን ለህዝቡ ለማስተዋወቅ የጀመረው በዚህ በቦካለማኮ/ዓሊተና የኢሮብ ተወካዮች ስብሰባ ላይ ነበር። ይህ ታሪካዊ ስብሰባ ተጠናቆ ህዝቡ ወደየአከባቢው ለመበታተን ሲዘጋጅ ነበር እነዚህ የተሓህት ታጋዮች የደረሱት። ታጋዮቹ ለህዝቡ ድርጅታችንን ከናንተ ጋር ለማስተዋቅ እንፈልጋለንና አንዴ አዳምጡን ብለው ጠየቁ። ህዝቡ መሽቶበት ወደየአከባቢው ለመሄድ ቸኩሎ ስለነበረ ሌላ ጊዜ የራሳችሁ ስብሰባ ጠርታችሁ ልታነጋግሩን ትችላላችሁ፣ አሁን ግን ስለመሸብን መሄድ አለብን ብሎ አንዳንዱ መሄድ ጀመረ። ይህን ጊዜ ሁለቱ የተሓህት ታጋዮች አቶ ገረይን እባክህ ህዝቡን ላጭር ደቂቃም ቢሆን መልእክታችን እንዲያዳምጠን አግባባልን ብለው ለመኑት። አቶ ገረይም እባካችሁ ላጭር ጊዜ አድምጡዋቸው ብሎ ህዝቡን ስለተማጸነ ህዝቡ እሺ ብሎ እንደገና ተመልሶ ተቀመጠ። ከሁለቱ አንዱም ተሓህት የሚታገልለት ዓላማ ይህ ነው በማለት እንደሚከተለው ባጭሩ አስቀመጠ።

1. ስማችን ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ ይባላል፣
2. የተሰለፍንለት መሰረታዊ ዓላማችን ደግሞ ባህላችን፣ ቋንቋችና ምንነታችን በአማራ ባህልና ቋንቋ ስለተረገጠ፣ ባህላችንና ቋንቋችንን እንዳናሳድግ በአማሮች ስለተከለከልን፣ ከዚህ የአማራ ጭቆና የትግራይን ህዝብ ነጻ ለማውጣት እየታገልን ያለን ልጆቻችሁ ነን።
3. ስለሆነም ከአማራ ጭቆና ተላቀን የራሳችን መንግሥት ለመመስረት በምናደርገው ትግል የናንተ የአባቶቻችን፣ ወንድሞቻችን ድጋፍና ተሳትፎ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ የትግራይ ህዝብን ከአማራ ጭቆና ለማላቀቅ በምናደርገው መራራ ትግል ከጎናችን እንድትቆሙ ለመጠየቅና ለመተዋወቅም ጭምር ነው ዛሬ እዚህ በመካከላችሁ የተገኘነው ብሎ ሃሳቡን ባጭሩ አቀረበ።

ይህ ከላይ የተቀመጠው የተሓህት አባል ንግግር ካዳመጡ በኋላ ያባ ዓዶዑማር ሓሊቦ የሚቀጥለውን መልስ ለህወሓት ታጋይ ሰጡ።

1. ልጄ በመጀመሪያ ስማችሁ ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ ከሚሆን ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ኢትዮጵያ ቢሆን በተሻለ ነበር።
2. በሁለተኛ ደረጃ አንተ በግልጽ እንዳስቀመጥከው እናንተ የምትታገሉት የትግራይ ባህልና ቋንቋ በአማራ ባህልና ቋንቋ ስለተረገጠ የትግራይ ቋንቋና ባህልን ከዚህ ከአማራ ጭቆና አላቃችሁ ትግራይን የበላይ ለማድረግ ነው።
3. በርግጥ እኛ የኢሮብ ህዝብ በትግራይ ጠቅላይ ግዛት የምንገኝ ህዝብ ነን። በባህልና በቋንቋ ጭቆናና ረገጣ ደረጃ ከተመጣ ደግሞ የኛ የኢሮብ ህዝብ ባህልና ቋንቋ የሚረገጠውና የሚጨቆነው በትግራይ ቋንቋና ባህል ነው።
4. አንተ እኛ ኢሮብ ከትግራይ ባህልና ቋንቋ የተለየ ባህልና ቋንቋ እንዳለን እንኳን አታውቅም ወይም አትቀበልም። ስለሆነ እኛ የኢሮብ ህዝብ እንድንሰማችሁና እንድንደግፋችሁ ከፈለጋችሁ መጀመሪያ በግልጽ ባህላችንና ቋንቋችን በትግራይ መጨቆኑን መቀበልና ይህም ጭቆና እንዲወገድ እንደምትታገሉ በግልጽ ማስቀመጥ አለባችሁ።
5. ስለ ባህልና ቋንቋ ጭቆና እንናገር ከተባለ፣ ከዚህ ባህላዊና የቋንቋ ጭቆና ለመላቀቅ እንታገል ከተባለ የኛ የኢሮብ ህዝብ መጀመሪያ መታገል ያለበት ሩቅ ያሉትን የማያውቃቸው አማራን ሳይሆን እዚህ ከጎረቤቱ በመሆን ባህሉንና ቋንቋውን የሚረግጠው የትግራይ ባህልና ቋንቋን ነው። እኛን ገና የኢሮብ ደንበር ተሻግረን ወደ ትግርኛ ተናጋሪዎች ሰፈር ስንደርስ ቋንቋችንና ባህላችን የሚሰደበው በትግርኛ ተናጋሪ ወንድሞቻችን ነው።
6. ስለሆነ የናንተ ዓላማ ለኛ ለኢሮብ ህዝብ የሚጠቅም ምንም ነገር የለውም። ድርጅታችሁና እኛ ብዙ የሚያገናኝን ነገር የለም ብለው ንግግራቸውን ጨረሱ። ልክ ያባ ዓዶዑማር ሓሊቦ እንዲህ ብለው ንግግራቸውን እንደጨረሱም ተሰብሳቢው ምንም ሃሳብ ሳይሰጥ ብድግ ብሎ ወደየአቅጣጫው ተበታተነ።

እንግዲህ ሃቁ ይህ ነው። ሃቁ ይህ ከላይ ያስቀመጥኩት ሆኖ እያለ አቶ ፀጋው ታደሰ በሚተርኩት "**ዘይተቐልዐ ታሪክ ህዝቢ ኢሮብ**" ውሰጥ የኢሮብ ህዝብ ገና ከጅምሩ ኢህአፓንና

ህወሓትን እኩል ተቀብሎ እኩል አስተናግዶአቸዋል ብሎ መተረክ ለምን ተፈለገ? የሚለው ጥያቄ በሚገባ መመርመርና ትክክለኛ መልስ ማግኘት ያለበት ጥያቄ ነው። በወቅቱ በቦካለማኮ ስብሰባ የነበሩ የኢሮብ ተወላጆች በሙሉ ባይባልም በህይወት አሉ። በተለይ ታሪክ እንደ ታሪክ በትክክል እንዲዘገብ የምትፈልጉ ሃቁን ለመናገር ደፈር በሉ። ወጣቶች ይህ የኣባቶቻችን ታሪክ ነው ተብሎ ሲነገር ዝም ብሎ መቀበል ሳይሆን እንዴት ብላችሁ ጠይቁ።

በመጨረሻም በአቶ ፀጋው ታደሰ የተተረከው "**ዘይተቐልዐ ታሪክ ህዝቢ ኢሮብ**" በሚለው የተንቀሳቃሽ ፊልም ሥራ ላይ ሁለት አስተያየቶችን ባጭሩ አስቀምጬ የዛሬውን መጣፍፌን እዘጋለሁ።

1ኛ. ይህ ትረካ ለምን በሳሆ ሊሆን እንዳልቻለ ብዙ ባይረዳኝም፣ አቶ ጸጋው ታደሰ በጥሩ አቀራረብ በርካታ ትክክለኛ የሆኑ ጥንታዊ በአፈታሪክ ደረጃ ከአባቶቻችን ስንሰማቸው የነበሩ ታሪካዊ ክንዋኔዎችን አስደምጠውናል። በዚህ ላመሰግናቸው እወዳለሁ።

2ኛ. አቶ ጸጋው ታደሰ ታሪኩን ሲተርኩ ሆን ተብሎ አሁን ስልጣን ላይ ያለ መንግስት ለማስደሰት በሚል ይመስለኛል በቅርብ ጊዜ ማለት ባለፉት 30ና 40 ዓመታት ውስጥ ስለተከናወኑ ድርጊቶች ሲተርኩ ታሪክን እንደ ታሪክ ሳይሆን ታሪክን ለፖሊቲካ ጥቅም ሲባል ወደ ህወሓት ያዳሉበት ሁኔታን በሚገባ ተመልክቻለሁ። በሚቀጥለው መጣጥፌም ከዚህ ከአቶ ፀጋው ታደሰ ትረካ በትክክል አልተተረኩም የምላቸውን ነጥቦች አንድ በአንድ በመልቀም እተችባቸዋለሁና የነገ ሰው ይበለን።

የካቲት 2003 ዓ.ም.